# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 253 መጋቢት 12 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ከወያኔ በጅጉ የተሻለ ስርዓት የሚገባን ህዝብና ሀገር እንደመሆናችን ህዝባችን በወያኔ አገዛዝ ላይ በቃኝ በማለት ዛሬውኑ እንዲነሳና ! በየአቅጣጫው ለነጻነት የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን እንዲቀላቀል ግንቦት 7 የፍትህ የነትጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የትግል ጥሪውን ያቀርባል!

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የመለስ ዜናዊ ራዕይና መተካካት ያልተንጸባረቀበት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ስብሰባ ተጠናቀቀ

የመለስን ራዕይ ከግቡ ሳናደርስ እንቅልፍ አይወስደንም ብለዉ ሲዝቱ የከረሙት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች "መተካካት" የሚለዉን ዋናዉን የመለስ ፖሊሲ ወደ ጎን ትተዉ ሰሞኑን በተከታታይ ባካሄዷቸው ስብሰባዎች በአብዛኛው ነባር አመራራቸዉን መርጠዉ ድህረ መለስ ጉዟቸዉን መጀመራቸዉን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ፡፡ በዚህ ባሳለፍዉ ሳምንት ዉስጥ አዋሳ፤ መቀሌ፤ አዳማና ባህርዳር ላይ በተካሄዱት የየፓርቲዉ ጉባኤዎች ላይ መለስ ዜናዊ መተካካት ብሎ የጀመረዉ ነባር የፓርቲ ሹማምንትን በአዲስ የመተከት ፖሊሰ እምብዛም በተግባር ባይዉልም አራቱም ድርጅቶች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አንዳንድ ነባር አባላቶቻቸዉን ከፓርቲዉ የስራ አስፈጻሚ ከሚቴ አስወግደዋቸዋል፤ በዚህም መሠረት ደአህዴን ተሾመ ቶጋን፤ ህወሀት ስዩም መስፍንን፤ብርሀኔ ገ/ክርስቶስንና አርከበ ዕቁባይን፤አህዴድ አባዱላ ገመዳን፣ ግርማ ብሩንና ኩማ ደመቅሳን ብአዴን ደግሞ ብርሃን ኃይሉን ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት አሰናብተዋቸዋል።

ሟቹ መለስ ዜናዊ በቀየሰዉ ዕቅድ መሰረት መተካካት እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ቀጥሎ ከ2007ቱ ምርጫ በሁዋላ ነባር የአመራር አባላት ሙሉ በሙሉ ይለቃሉ ተብሎ የተገመተ ቢሆንም በሰሞኑ የፓርቲዎች ስብሰባ እንደታየዉ ግን ነባር ታጋዮች ስልጣናቸዉን እንደያዙ እንዲቀጥሉ ተደርፈጓል። በ2003 ዓ.ም በተደረገዉ የመተካካት ሹምሽር የኃላፊነት ቦታዉን አጥቶ የነበዉ የብአዴኑ አዲሱ ለገሰ ተመልሶ ወደ ስልጣን የመጣ ሲሆን በቅርቡ በወጣት መሪዎች ይተካሉ ተብሎ ሲጠበቅ የነበረዉ በረከት ስምኦን፤ ህላዊ ዮሴፍና፣ አባይ ወልዱ ጭራሽ ስልጣናቸውን እያጠናከሩ መምጣታቸዉ ታዉቋል።

በ2003 ዓም በተደረገዉ መተካካት የመንግስትና የፓርቲ ኃላፊነታቸውን የለቀቁት ስዩም መስፍንና ሌሎች ዘጠኝ የህወሃት አባላት ከጤና ጋር በተያያዘ በራሳቸው ፈቃድ ድርጅቱን ለመልቀቅ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የተሰናበቱ ሲሆን የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ግን የእነዚህን ሰዎች መሰናበት ከመተካካት ጋር አያይዞ ዘግቧል። በአጠቃላይ ብዙ ዉጣዉረድና ድራማ የታየበት የዘንድሮዉ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ስብሰባ ሲጀመር የመለስ ዜናዉን ራዕይ ከግቡ እናደርሳለን በሚል መሪ ቃል የተጀመረ ሲሆን ሲፈጸም ግን በመርገጥ "መተካካት" የሚለዉን የድርጅቱን መስራች አላማና ራዕይ በሌላ ነገር በመተካት ተፈጽሟል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ለአቤቱታ የመጡ የደቡብ ክልል ዜጎች መታገታቸው ተዘገበ

የተለያዩ የመብት ጥያቄዎችን ለመጠየቅ በደቡብ ክልል በቁጫ ወረዳ ለአቤቱታ የወጡ ከ1000 ያላነሱ ሰዎች በፖሊስ ታግተው መዋላቸውን የአካባቢው ሰዎችን ዋቢ በማድረግ ኢሳት ዘግቧል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ከፍትህ፣ ከመልካም አስተዳዳር እና ከመብት እጦት ጋር በተያያዘ በርካታ ጥያቄዎችን ላለፉት 8 አመታት ሲያቀርቡ የቆዩት የቁጫ ወረዳ ነዋሪዎች፣ 7 ወኪሎቻቸው መታሰራቸውን በመቃወም ትናንት አቤቱታ ለማቅረብ ሲሰባሰቡ በፌደራል ፖሊሶች መታገታቸው ከነኝህም ታሳሪ ዜጎች ድበደባ የደረሰባቸው ሰዎች መኖራቸውም ታውቋል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ጉዳዩን በማስመልከት ጥያቄ ያቀረበላቸው የአንድነት ፓርቲ የደቡብ ክልል ተወካይና የምክር ቤት የሆኑት አቶ ዳንኤል ሽበሺ በክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች የሚታየው ችግር የቆየ መሆኑን አውስተው፣ የትናንትናው ተቃውሞ ግን የሽማግሌዎች መታሰር መሆኑን ገልጸዋል።

ኢሳት አክሎ እንደዘገበው አቶ ዳንኤል በሰላም በር የታሰሩት ሰዎች ህዝብን ታነሳሳለችሁ ተብለው መሆኑን መግለጻቸውን በአጠቃላይ በክልሉ ያለው የመልካም አስተዳደርና ፍትህ እጦት መባባሱን ጠቅሷል።

የአገር ሽማግሌዎች ለምን ታሰሩ? ለአቤቱታ የመጡ ሰዎችስ ለምን ታገቱ በማለት ኢሳት ጥያቄ ያቀረበለት የወረዳው ፖሊስ አዛዥ ሻለቃ አኒሳ ፣ ሰዎቹ ጥያቄ ያቀረቡበት መንገድ አግባብ አይደለም በሚል መታሰራቸውን አምኖ፣ ሰልፈኞቹ የመጡበት መንገድ ተገቢ ባለመሆኑ እንደመለሱዋቸውም ተናግረዋል ብሏል ኢሳት።

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የባህር ዳሩ ጊዮን ሆቴል ህወሀትንና ብአዴንን ዱላ ቀረሽ ፍጥጫ ዉስጥ መክተቱ ተሰማ

በደርግ ዘመነ መንግስት የአገር ሀብት የነበረዉና ባለፉት ሃያ አንድ አመታት የትግራይ ተወላጅ በሆነ ግለሰብ አላግባብ ተይዞ የነበረዉ የባህርዳሩ ጊዮን ሆቴል ባለቤትነት ለአማራ ክልል የመንግስት ቤቶች ኤጄንሲ እንዲዘዋወር መወሰኑ የህወሀትንና የብአዴንን ከፍተኛ ባለስልጣኖች ግጭት ዉስጥ እንዳስገባ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸዉ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩልን ዜና ገለጹ።

በ1983 ዓ.ም ወያኔ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በመንግስት ይዞታ ስር የነበረዉን የባህርዳሩን ጊዮን ሆቴል ለመለስ ዜናዊ የቅርብ ዘመደ ለሆነዉ ወልዱ ለሚባል ግለሰብ በ5000 ብር በኪራይ ስም መሸለሙ ይታወሳል። የአድዋ ተወላጅ የሆነዉ ወልዱ የሚባለዉ ግለሰብ ወያኔ የትጥቅ ትግል ያካሄድ በነበረባቸዉ 17 አመታት ባህርዳር ዉስጥ የህወሀት ሰላይ እንደነበረ የሚታወቅ ሲሆን መለስ ዜናዊ ያንን የመሰለ ዘመናዊ ሆቴል በ5000 ብር የሸለመዉ ለዚሁ የስለላ አገልግሎቱ እንደሆነ ብዙ የባህር ዳር ነዋሪዎች በግልጽ ይናገራሉ።

ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ጊዮን ሆቴል ለወልዱና ለልጁ ለብስራት ወልዱ እጅግ በጣም ከፍተኛ ትርፍ ሲያስገኝ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን ይህ በሆነባቸዉ አመታት ሁሉ የባህርዳር ከተማ ህዝብ አንድ ኪዎስክ በ5 ሺ ብር እየተከራየ እንዴት ጊዮን ሆቴልን የሚያክል ትልቅና ዘመናዊ ሆቴል በ5 ሺ ብር ብቻ ይከራያል እያለ ተቃዉሞዉን ቢያሰማም የሚሰማዉ ጠፍቶ ሃያ አመታት አልፈዋል። ሆኖም በቅርቡ መለስ ዜናዊ ከሞተ በኋላ የፌደራል የኪራይ ቤቶች ድርጅት የአማራ ክልል መንግስት ሆቴሉን እንዲረከብ ለአማራ ክልል የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ደብዳቤ በመጻፉ ጉዳዩ ከክልል አልፎ ገዢዉ ፓርቲ ጽ/ቤት መድረስ ችሏል። ሆቴሉን ለክልል መንግስት እንዲያስረክቡ ደብዳቤ የደረሳቸዉ ወሌደና ሌጁ ብስራት ጉዳዩን በቀጥታ ለበረከት ስምኦን፤ ለፌዳሩሽን ምክር ቤት ሰብሳቢው ካሳ ተክለብርሀንና ለአዲሱ ለገሰ የመለስ ዜናዊን ሞት ተክትል ሆቴሉን እንዱያስረክቡ መጠየቃቸውን በመናገራቸው፣ ባለስልጣኖቹ የክልሉ መንግስት የጻፈውን ደብዳቤ እንዱያነሳ ጠይቀዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከሳሊኒ በመቀጠል የህዳሴ ግድብ ተብየው ተጠቃሚው የአዜብ መስፍን ቤተሰብ ድርጅት መሆኑ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴላቪዥን ኢሳት ቀደም ብሎ ከሁለት አመታት በፊት በአዜብ መስፍን የእህት ልጅ አቲኮ ስዩም አምባየ የተመሰረተው ኦርቺድ ቢዝነስ ግሩፕ በጣሊያኑ ሳልኒ ኮንስትራክሽን አማካኝነት በሚገነቡት ግልገል ጊቤ አንድ እና ግልገል ጊቢ ሁለት የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ፕሮጀክቶች ስሚንቶ እና የግንባታ እቃዎችን እንዱሁም ከፍተኛ ማሺነሪዎችን በማቅረብ ከፍተኛ የሆነ ትርፍ ማጋበሱን መዘገቡን አውስቶ ይሄው ኩባንያ ከሳሉኒ ጋር ግልጽነት የጎደለው የቢዝነስ ስምምነት በማድረግ በአሁኑ ጊዜ ለግንባታው የሚያስፈልገውን ስሚንቶ እንዱሁም ከባድ ማሺኖችን በማቅርብ ላይ እንደሚገኝ አጋልጧል።

ኢሳት በአባይ ወንዝ ላይ የሚሰራውን የህዳሴውን ግድብ ፕሮጀክት በቅርብ የሚያውቁ ሰዎችን ዋቢ በማድረግ እንደዘገበው ግድቡን እየገነባሁ ነው ከሚለው ሳልኒ በመቀጠል ከፍተኛ የሆነ ትርፍ የሚያገኘው ኦርቺድ፣ ከየትኛውም ድርጅት ጋር ሳይወዳደር በእነ አዜብ መስፍን አማካኝነት የስሜንቶና ማሽንሪዎች አቅራቢ ሆኖ ቀርቧል ብሏል።

ይሄው ኩባንያ ቦዲ ዋይዝ ጂም፣ ካፌ ፓኒኒ፣ ኦርቺድ ጄኔራል ኮንትራክተር፣ ኦርቺድ ትራንስፖርት፣ ኦርቺድ ትራንዚት፣ ኦርቺድ ማሽነሪ ሬንታል፣ ኤስ ኤንድ ኤስ እርሻ፣ ሂላል ቱር ኤን ትራቭል፣ ሜትሮሉክስ ፍላወር፣ ናይል ስፕሪንግ ውሀ፣ ሬንቦው ጊፍት ሾፕ፣ ሪል ሳልን፣ ወንደር ዊሌ ቢዝነስና ሌሎችም በአዲስ አበባና በመላው አገሪቱ ታዋቂ የሆኑ የንግድ ድርጅቶችን በስሩ አቅፎ መያዙን ኢሳት በማያያዝ ዘግቧሌ።

አቲኮ ስዩም ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ይህ ነዉ የሚባሌ ኃብት እንዳልነበራት ታሪኳን ያጠኑ ዘጋቢዎቹ ማረጋገጣቸውን የዘገበው ኢሳት ባለፉት 20 አመታት ግን በልዩ ትዕዛዝ "ኦርቺድ" ቢዝነስ ግሩፕ የሚባል ድርጅት ተከፍቶላት ሆን ተብሎ አያሌ የግንባታ ጨረታዎችን አንድታሸንፍና በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለ ቱጃሮች ተርታ ለመመደብ እንደቻለች መግለጹን አውስቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ/ኢህአዴግ ጉባኤ ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ

ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይና በተለምዶ ተለጣፊ እየተባሉ የሚጠሩት ሎሌ ድርጅቶቹ ሰሞኑን በጉባኤ ሽርጉድ ላይ ተጠምደዋል። የድግሱ፣ የፌስታውና የካርኔባሉ አይነትና ብዛት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች በቀን አንድ ጊዜ ለመብላት በሚቸገሩበት ሀገር ውስጥ የሚደረግ አይመስልም። ይሔው የፈረደበት የኢትዮጵያ ድሃ ግብር ከፋይ ይህን በብዙ መቶ ሚሊየኖች ብር የሚቆጠር ወጭ ይሸፍናል። ማን ከልካይና ጠያቂ አለ? ሌሎች በህግ የተመዘገቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ለአንድ ደቂቃ እንኮን በአጠገቡ ዝር እንዳይሉ የሚከለክለው የመንግስት ሚዲያ ይህንን የግፈኞች የውሸት ዲስኩርና ፌሽታ በቀን 24 ሰአት ያጋፍራል። እንጨት እንጨት የሚል ፕሮፖጋንዳ ሲግተን፣ ሲያደነቁረን ይታገላል፡፡ ልብ ብሎ ለተመለከተው ጠቅላላው የወያኔ የጉባኤ ሽርጉድ ከጆርጅ ኦርዌል "የእንስሳት እርሻ" (Animal Farm) የስላቅ ድርሰት ተወስዶ የሚሰራ ትያትር ይመስላል።

የወያኔ መሪዎችና ሎሌዎቻቸው ለሆድ አደሮች እግዚያብሄር እንደ ፀጋ ሰጥቷቸዋል። እፍረትና ይሉኝታ የሚባል ነገር ከልክሎ ፈጥሯቸዋል። ትዝብት አይፈሩም። ህዝቡ አንጀቱ እያረረ እብሪታቸውን ሲመለከት በደስታ ፈንድቆ የሚጨፍር ይመስላቸዋል። ኢትዮጵያን ወደ ፖሊሲያዊ መንግስትነት ቀይሮ የሞተውን አለቃቸውን ለአፍሪካና ለአለም የሚያጎድል መሪ ነው ይሉናል። መለስ በምን ህመም እንደሞተ እንኳዋን አጣርተው የማያውቁ ጀሌዎች ትግል ላይ የተሰዋ ኣርበኛ ኣስመስለው ሲያወሩ አያፍሩም።

ይህንኑ እንዲመሰክርላቸው ከዚህ ቀደም በሙሁር ሽቃጭነት (intellectual prostitution) የገዛ ጎደኞቻቸው ሙሁር ከከሰሳቸው የኮሎምቢያ ሙሁራንም አንዱን አስመጥተዋል። በነዚህ ሰዎች ግምት መለስ ዜናዊ በግፍ የጨፈጨፋቸው ወገኖቻችን፣ የዝምብ ያህል ክብር የላቸውም። በእስር የታሰሩት ንጹሃንና ሀገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ወገኖቻችን በነሱ ቤት ሰዎች አይደሉም። እናም ጉባኤው አይናችሁን ጨፍኑልንና እናሞኛችሁ ከሚል ቡዋልት የተለየ አይደለም።

እንዳለፉት ጉባኤዎች ሁሉ የዚህንም ጉባኤ ተብዬ ውጤት አስቀድሞ መናገር ይቻላል።አሁንም አይናቸውን አጥበው ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እየሰራን ነው የሚል መግለጫ ያወጡልናል። መለስ ዜናዊ ቀድሞውኑ ራሱን አዋቂ አድርጎ በመሳል ከሱ የተቀራረበ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ሁሉ ጠራርጎ በደካሞች ራሱን ከቦ ከበሮ እያስደለቀ መቆየቱ ለከንቱ የሙት ውዳሴ ጠቅሞታል። እነዚህ ደካማ ጀሌዎች አሁንም ምንም የራሳቸን እውቀት ስለሌለን በሞተው መለስ ራእይ በሚሉት ነገር እንደሚመሩ በጉባኤው መጨረሻ የአዞ እንባ ያለበት መግለጫ ያወጣሉ።

እድገትና ትራንስፎርሜሽን የሚባለው ነገር ከሁለት አመት በኋላ ህብስተመና ከሰማይ ይወርዳል የሚል የጉባኤ ውሳኔም እንሰማለን። መብታቸውን የሚጠይቁ ኢትዮጵያውያንን ለማስፈራራትና አስጎንብሶ ለመግዛት ይጠቅማሉ የተባሉ መግለጫዎችም በጉባኤው መጨረሻ ይጠበቃሉ። አሸባሪ፣ ጸረ-ልማት፣ አክራሪ፣ ወዘተ ወዮላችሁ ይሉናል። ስልጣንና ስልጣንን መከታ በማድረግ የዘረፉት ሀብት ይቀርብናል የሚል የሚያባንን ፍርሃት ስላደረባቸው ባስፈራሩን ቁጥር ሰላም ያገኙ ይመስላቸዋል። በህዝብ መሃል ልዩነት መፍጠርና አንዱን በአንዱ ላይ ማነሳሳት ሰላም ይሰጠናል ብለው ስለወሰኑ እርስበርሳችን እንድንጋጭ ጥሪ ያቀርቡልናል።

ዛሬም እንዳምና ካቻምናው የነሱ ምኞት ስለጨመረና ስለተመቻቸው ኢኮኖሚው እየተመነደገ ነው እንደሚሉን ይጠበቃል። የህዝባችን ኑሮ የከዘራ ያህል እንኳን ቀና እንዳላለ ህዝቡ ራሱ ያውቀዋል።

ወገን ይሄ ግፍ ለከቱን አልፏል። ከወያኔ አገዛዝ በጎ ነገር መጠበቅ ከእባብ እንቁላል ርግብ መጠበቅ መሆኑን ካወቅን ውለን አድረናል።

ግንቦት 7 የፍትህ የነትጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሀገራችን ዴሞክራሲ ሰፍኖ በገዛ ሀገር ተዋርዶ መኖር ቆሞ፣ በኩራትና በሰባአዊ ክብር ሁላችንም የምንኖርበት ሀገር ወያኔና ሎሌዎቹ ሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው ብሎ ያምናል ። በመሆኑም የወደፊቱ እጣችንና ተስፋችን ያለው በራሳችን መዳፍ ውስጥ ብቻ እንደመሆኑ ለነጻነቱና ለክብሩ ቀናዕ የሆነ ሁሉ በራሱ አነሳሽነት ትግሉን ለማቀጣጠል መነሳት ያለበት ጊዜው አሁን ነው ።

ከወያኔ በጅጉ የተሻለ ስርዓት የሚገባን ህዝብና ሀገር እንደመሆናችን ህዝባችን በወያኔ አገዛዝ ላይ በቃኝ በማለት ዛሬውኑ እንዲነሳና ! በየአቅጣጫው ለነጻነት የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን እንዲቀላቀል ግንቦት 7 የፍትህ የነትጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የትግል ጥሪውን ያቀርባል!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## የመለስ ዜናዊ ራዕይና መተካካት ያልተንጸባረቀበት የኢህአዴግ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በአንድ ጊዜ መልቀቂያ ማቅረባቸው አጋጣሚ ሳይሆን ከመለስ ህልፈት በሓላ በህወሃት ውስጥ ከተፈጠረው ልዩነት ጋር በተያያዘ ሳይሆን እንደማይቀር ምንጫችን ቢጠቅስም ይህን በተመለከተ ለማረጋገጥ ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም፡፡ ብዙዎች እንደሚገምቱት ከአርከበ እቁባይ ጋር ጤነኛ ግንኙነት ያልነበራት አዜብ መስፍን በዚህ ጉባኤ በድል አድራጊነት ወጥታለች።

ከፊታችን ቅዳሜ መጋቢት 14 ቀን እስከ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በባህርዳር ከተማ የሚካሄደው የኢህአዴግ ጉባዔ ኃይለማርያም ደሳለኝን በሊቀመንበርነት፣ ደመቀ መኮንን በምክትል ሊቀመንበርነት በድጋሚ ይመርጣል ተብሎ እንደሚጠበቅ ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

የወያኔ ኢህአዴግ ድርጅቶች ያደረጉትን ሹም ሽር በተመለከተ ጥያቄ ያቀረብንላቸው አንድ የቀድሞ የህወሀት ነባር ታጋይ፡ ምርጫውን "ውሀ ቢወቅጡት ነው" ብለውታል። "ከእነዚህ ሰዎች ምንም የሚጠበቅ ነገር የለም፣ ምን አዲስ ነገር እንደማይፈጥሩም ይታወቃል። የአፈና ስርአቱ እንደሚቀጥል ጥሩ ማሳያ ነው" ብለዋል ታጋዩ።

## የባህር ዳሩ ጊዮን ሆቴል ህወሀትንና ብአዴንን ዱላ ቀረሽ ፍጥጫ ዉስጥ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የክልሉ የመንግሰት ቤቶች ኤጀንሲ ጉዲዩ ከፍተኛ ዝርፊያ መሆኑን ገልጾ ዉሳኔዉን ለመለወጥ ፈቃደኛ አለመሆኑን ቢገልጽም የሆቴለ አስተዳዳሪ የሆነዉ ብስራት ወልዱ የክልሉን ባለስልጣናት በማስፈራራት እርምጃ እንደሚወስድ በመዛት ሆቴሉን ለማስረከብ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ገልጿል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የዝግጅት ክፍላችን በስልክ ያናገረዉ አንድ የኪራይ ቤቶች ድርጅት ሰራተኛ የሆቴሉ አስተዳዳሪ ብስራት ወልዱ ሆቴሉን እንዲያስረክብ ደብዳቤ ሲጻፍለት "ዋጋህን ታገኛለህ" የሚል መልስ መስጠቱን ተናግሯል። የባህርዳር ከተማ ህዝብ የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በአንድ ተራ የህወሀት አባል መደፈረቸዉን አስመልክቶ እያሾፈ ሲሆን እንደ ብዙ ታዛቢዎች እምነት የክልሉ መንግስት ከዚህ አይነቱ ህዝባዊ ትችት ነጻ መሆን የሚችለው ግለሰቡ ሆቴሉን እንዱያስረክቡ ሲያደርግና እንደማንኛውም ሰው ተጫርቶና ለጨረታዉ ተገቢውን ክፍያ ማስከፈል ሲችል ብቻ መሆኑ ታውቋል።

## ከሳሊኒ በመቀጠል የህዳሴ ግድብ ተብየው ተጠቃሚው የአዜብ መስፍን ቤተሰብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የህወሀት/ኢህአዴግ ባለስልጣናት በዘመዶቻቸው ስም የሚገነቧቸው የቢዝነስ ተቋማት እየተበራከቱ መምጣቱን በተደጋጋሚ ሲዘግብ እንደነበር ያስታወሰው ኢሳት የባለስልጣናትን የሀብት ምዝገባ ጨርሶ በአጭር ጊዜ ይፋ አድረጋለሁ በማለት ሲፎክር የነበረው ጸረ ሙስና ኮሚሽንም ቃሉን ለመጠበቅ እንደተሳነውና ኮሚሽኑ ባለስልጣናቱ በዘመድቻቸው ስም የያዙትን ሀብትና ንብረት ለመመዝገብ ስልጣን እንዳልተሰጠው ገልጿል።

# ኬንያ , , , , , , , ቆመን ጠበቅናት ጥላን አለፈች

“አለም አቀፉ ህብረተሰብ የኬንያን ሉዓላዊነትና የኬንያዉያንን ዲሞክራሲያዊ ዉሳኔ ያከብራል የሚል ሙሉ እምነት አለን፤ ከአሁን በኋላ የአፍሪካዉያን የወደፊት እድል የሚወሰነዉ በእኛዉ በአፍሪካዉያን ብቻ ይሆናል”

ይህንን ከዚህ በላይ የተቀመጠዉን የኬንያዉያንን በራስ መተማመንን የሚያመለክት ንግግር ያደረጉት በቅርቡ የኬንያ ፕሬዚዳንት ሆነዉ የተመረጡት ኡሁሩ ኬንያታ ናቸዉ። እንደ ፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በ2007 ዓም የተካሄደዉ የፕሬዚዳንትነት ምርጫና ዉጤቱ በፈጠረዉ ትርጉም የለሽ ግጭት ከ1500 በላይ ዜጎቿን ያጣችዉ ጎረቤታችን ኬንያ ከ2007 በኋላ በነበሩት አምስት አመታት ዉስጥ አዲስ ህግ መንግስት አርቅቃና ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነጻ የሆነ የፍትህ ተቋም ገንብታ በቅርቡ አለምን ያስደነቀና ከ2007ቱ ጋር ሲወዳደር “እንከን የለሽ” ሊባል የሚችል ምርጫ አካሂዳ በ50 አመት የነጻነት ታሪኳ ዉስጥ ለመጀመሪያ ግዜ ነጻና ሠላማዊ በሆነ ምርጫ መሪዋን መርጣለች። በቀድሞዉ ኢትዮጵያ ንጉስ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ድፕሎማሲያዊ ድጋፍና እርዳታ አበ1955 ዓም ነጻነታቸዉን የተቀዳጁት ኬንያዉያን እኛ ኢትዮጵያዉያን በ3000 አመት የነጻነት ታሪካችን ማድረግ፤ ማየትና መስማት ያልቻልነዉን ግዙፍ ዲሞክራሲያዊ ድል እነሱ በ50 አመት የነጻነት ታሪካቸዉ ማድረግ ችለዋል። የኬንያ ህዝብና የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዚህ አይነቱ አንጸባራቂ ድል የበቁት የኬንያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተዋህደዉ ወይም በመካከላቸዉ የሚገኙ ልዩነቶችን አስወግደዉ አይደለም፤ወይም የምርጫዉን ወቅት በተመለከተ ብቻ አብረን እንስራ የሚል የፖለቲካ መሞዳሞድ ተሞዳምደዉም አይደለም። የኬንያ ህዝብ እንደዚህ አይነቱን ነጻና ሰላማዊ ምርጫ ማካሄድ የቻለዉ ካለፈዉ ስህተቱ ተምሮ ነጻና ገለልተኛ የፍትህ ተቋም፤ ነጻ የሚዲያ አዉታርና የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸዉን ኬንያዉያን በእኩልነት ማስተናገድ የሚችል ገለልተኛ የምርጫ ተቋም መመስረት በመቻላቸዉ ነዉ። በአጠቃላይ ኬንያዉያን በቅርቡ ለታዘብነዉ ከፍተኛ ድል የበቁት ከዚህ ቀደም እንደዚህ አይነቱን ህዝባዊ ድል እንዳያዩ እንቅፋት የሆኑባቸዉን ተቋሞች አፍርሰዉ በምትካቸዉ ሁሉን አቀፍ ተቋም መገንባት በመቻላቸዉ ነዉ።

የሚገርመዉ የኬንያ የፖለቲካ መድረክ በዚህ አንጸባራቂ ድል ያገኘዉ ትልቅ ነገር ቢኖር አዲስ የፖለቲካ ሰዉ ሳይሆን አዲስና ጤነኛ የፖለቲካ ህደት ነዉ። ሁለቱ ከፍተኛና እልህ አስጨራሽ ፍክክር ያሳዩት ተወዳዳሪዎች ማለትም አሸናፊዉ ኡሁሩ ኬንያታና ተሸናፊዉ ራይላ ኦዲንጋ ለኬንያ ፖለቲካ መድረክ አዲስ መጦች አይደሉም። ሁለቱም የአዲስቱ ኬንያ መስራቾች ልጆች ናቸዉ። ኡሁሩ ኬንያታ የመጀመሪዉ የኬንያ ፕሬዚዳንት የጆሞ ኬንያታ ልጅ ሲሆኑ ራይላ ኦዲንጋም የመጀመሪያዉ የኬንያ ምክትል ፕሬዚዳንት የጃራሙጊ ኦጅንጋ ኦዲንጋ ልጅ ናቸዉ። ሁለቱም ተንደላቅቀዉ ያደጉ፤ የተማሩና የናጠጡ ኃብታሞች ናቸዉ። ደግሞም ሁለቱም ከዚህ ቀደም ለፕሬዚዳንትነት ተወዳድረዉ ያልተሳካላቸዉ ናቸዉ። በሁለቱ መካከል ልዩነት ቢኖር የ68 አመቱ ኦዲንጋ የሉዎ ብሔረሰብ የ53 አመቱ ኡሁሩ ደግሞ የኪኩዩ ብሔረሰብ ተወላጆች መሆናቸዉ ነዉ።

ኬንያ በእድገት ከኢትዮጵያ የምትሻል አገር ብትሆንም ምድቧ እንደ ኢትዮጵያ በእድገት ወደኋላ ከቀሩ አገሮች ተርታ ነዉ። ኬንያ እንደ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦች አገር ናት። ኢትዮጵያ ዉስጥ በብሔር ብሔረሰቦች መካከል የሚታየዉ ብጥብጥ ኬንያ ዉስጥም ይታያል። ይህንን ለማየት ደግሞ ብዙ መጓዝ አያስፈልግም፤ በቅርቡ በኡሁሩ ኬንያታና በራይላ ኦዲንጋ መካከል የታየዉን ዱላ ቀረሽ የምርጫ ፍክክርና ከበስተጀርባቸዉ የተሰለፈዉን ህዝብ ዞር ብሎ መመልከቱ ይበቃል። የሚገርመዉ ኪኩዩዎች የሚያመልኩት ጆሞ ኬንያታና የሉዎ ብሔረሰብ አባላት የሚኮሩበት ኦጂንጋ ኦዲንጋ በግዜያቸዉ ከፍተኛ የፖለቲካ ፍጥጫ ዉስጥ የገቡ ሰዎች ነበሩ። ፍጥጫዉ ደግሞ ልክ እንደ ዛሬዉ በሁለቱ ሰዎች መካከል ብቻ ሳይሆን በኪኩዩና በሉዎ ብሔረሰቦች መካከል በግልጽ የሚታይ ፍጥጫ ነበር። ይህ ፍጥጫ ዛሬም እንዚህ ሁለት የኬንያ መስራች አባቶች ከሞቱ ከአመታት በኋላ በልጆቻቸዉ ቀጠለ እንጂ አልበረደም። ዘንድሮ ግን ለመጀመሪያ ግዜ መሉ ለሙሉ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ይህ በሁለቱ የኬንያ ግዙፍ ብሔረሰበች መካከል የሚታየዉ የፖለቲካ ፍጥጫ ህግ ሊገዛዉ በሚችል ድባብ ዉስጥ የገባ ይመስላል። በእርግጥም የዘንድሮዉ የኬንያ ምርጫ ከምን ግዜዉም በበለጠ መልኩ ነጻና ሰላማዊ ምርጫ ነበር፤ ይህ እንዲሆን ደግሞ የኬንያ ህዝብና የፖሊቲካ መሪዎች ከፍተና መስዋዕትነት ከፍለዋል።

ኬንያና ኢትዮጵያ ከቅርብ ጉርብትና ባሻገር ብዙ ታሪካዊና ማህበራዊ እሴቶችን የሚጋሩ አገሮች ናቸዉ። ከላይ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ሁለቱ አገሮች አያሌ ብሔረሰቦች ጎን ለጎን የሚኖርባቸዉ አገሮች ናቸዉ። ሆኖም የኬንያ ፖለቲካ በተለይ የምርጫ ፖለቲካቸዉ ከፍተኛ የብሔር ማንነት የሚንጸባረቅበት ቢሆንም የኬንያ ማህበረሰብ መሠረት የተገነባዉ በዜግነት ላይ ነዉ እንጂ እንደ ወያኔዋ ኢትዮጵያ በብሔር ብሔረሰቦች ማንነት ላይ አይደለም። በወያኔዋ ኢትዮጵያ ዕድሜያቸዉ 35 እና ከ35 አመት በታች የሆነ ኢትዮጵያዉያን ማንነታቸዉን የሚገልጹት ኢትዮጵያዉያን ነን ብለዉ ሳይሆን እኔ ኦሮሞ፤ አማራ፤ ትግሬ ፤ ወላይታ፤ ጉራጌ ወዘተ እያሉ ነዉ። ጎረቤታችን ኬንያዉያን ግን አድገዉ ለአዋቂነት የሚበቁት እኔ ኪኩዩ ነኝ፤ ማሳይ ነኝ ወይም ካለንጂኒ ነኝ እያሉ ሳይሆን እኔ ኬንያዊ ነኝ እያሉ ነዉ።

የኢትዮጵያን ህዝብ በ1997 ዓም ማግስት ለብልቦ የፈጀዉ የአግአዚ የጅምላ ግድያ አባዜ ኬንያንም በ2007 ምርጫ ወቅት መለብለብ ብቻ ሳይሆን አቃጥሎ ፈጅቷታል። እኛ ኢትዮጵያዉያን ከ1997ቱ ምርጫ ጋር በተያያዘ ከ200 በላይ ሠላማዊ ዜጎች በየጎዳናዉ ላይ በአልሞ ተኳሽ አግአዚዎች ተገድለዉብናል። የኬንያም ህዝብ በ2007ቱ ምርጫ ከ1500 በላይ ወንድሞቹንና እህቶቹን አጥቷል። ሁለታችንም ተጎድተናል። የምንለያይበት ነገር ቢኖር ሁለት መቶዎቹ ኢትዮጵያዉያን የተጨፈጨፉት ህዝብ “መረጠኝ” በሚል መንግስት ሲሆን ኬንያ ዉስጥ ግን ያን ያክል ሰዉ ያለቀዉ የተለያዩ የኬንያ ብሔረሰቦች ዪኔ ነዉ የሚሉት ሰዉ ባለመመረጡ በፈጠሩት ግጭት ነዉ።

የኬንያ ህዝብ አገሪቱ በ2007 ዓም ከደረሰባት እልቂት የኬንያ የፖለተካ ፓርቲ መሪዎች ደግሞ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ከፈጸሙት ስህተት ተምረዉ ጎራ ለይቶ መተላለቅንና መጠፋፋትን የሚያስወግድ አዲስ ህገ መንግስት አርቅቀዉና ገለልተኛ ነጻ የምርጫ ተቋም ገንብተዉ ነጻና ሰላማዊ ምርጫ ማካሄድ ችለዋል። እኛ ግን በ1997 ዓም ከ200 በላይ ወገኖቻችንን አስገድለን እንደገና በ2002 ዓም በየቦታዉ ሰዎች አስገድለን ምንም ነገር ባልተቀየረበትና ነጻ ፍርድ ቤት፤ ገለልተኛ የምርጫ ተቋምና ለማንም ያልወገነ ነጻ ሜድያ በሌለበት ሁኔታ እንደገና ሌላ ህይወት ለመገበር ምርጫ ከሚሉት የወያኔ አሻንጉሊት ጋር አሁንም እንደተቃቀፍን ነዉ።

እኛም ሆንን ኬንያዉያን ነጻ የምርጫ ቦርድ፤ ነጻ ፍርድ ቤትና ነጻ ሜዲያ በሌሉበት ቦታ የህዝብን የስልጣን ባለቤትነት ማረጋገጥ በፍጹም እንደማይቻል ከተረዳን ቆይተናል፤ የሁለቱም አገሮች ህዝብ መሪዉን በነጻነት መምረጥ የሚያስችሉትን ተቋሞች ለመገንባት ትግል ከጀመረ ቆይቷል። ታዲያ በእኛ ድጋፍና እርዳታ ነጻነታቸዉን የተቀዳጁት ኬንያዉያን ህግመንግስታቸዉን አሻሽለዉ፤ ከፖለቲካ ተጽዕኖ የጸዳ የፍትህ ተቋም መስርተዉና በነጻነት ሁሉንም እኩል የሚያገለግል የሜድያ አዉታር ዘርግተዉ መሪያቸዉን በነጻነት ለመመምጥ ሲበቁ እኛ ምን ነካን? ነጻነትን ከኬንያዉያን ነዉ የምንማረዉ ወይስ እነሱ ናቸዉ ከእኛ የሚማሩት? በነገራችን ላይ ባለፈዉ ሳምንት በነጻ ምርጫ ተወዳዳሪዉን አሸንፎ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ኬንያን የመምራት እድል ያገኘዉ ኡሁሩ ኬንያታ ሲወለድ አገሩ ኬንያ ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ገና ነጻ አልወጣችም ነበር። የእኛ የኢትዮጵያዉያን ነጻነት ሲወራ ግን ኬንያን የገዙት እንግሊዞች እራሳቸዉ በአገርነት አይታአወቁም ነበር። ታድያ ኬንያዉያን ባህር ተሻግረዉ መጥተዉ ከገዟቸዉም ሆነ አገር ዉስጥ ሆነዉ የረገጧቸዉን ጨቋኝ መሪዎች አስወግደዉ ሰብዓዊ መብታቸዉንና ነጻነታቸዉን ሲያስከብሩ እኛ ምን ነክቶን ነዉ ሀያ አንድ አመት ሙሉ እፍኝ በማይሞሉ ሰዎች አንገታችንን ደፍተን የምንገዛዉ?

ለምንድነዉ ዘረኞች እንዳሰኛቸዉ ሲያስሩንና ሲገድሉን አፋችንን ዘግተን የምንመለከታቸዉ? እስከመቼ ነዉ በዉድቅት ሌሊት በራችንን ሰብረዉ እየገቡ የሚያሸብሩን? ለመሆኑ እንሱ ማን ሆነዉ ነዉ እናትና ልጅ፤ ባልን ሚስት ፊት በጥፊ እየመቱ አንጠልጥለዉ የሚወስዱት? እኮ እነሱ ማናቸዉና ነዉ ልጅን ከእናት ሚስትን ከባል የሚነጥሉት? አሁንማ የእኛዉ የእራሳችን ፍርሀትና ዝምታ ጭንቅላታቸዉን በትምኪት ልባቸዉን በትዕቢት ሞልቶት ጭራሽ ከሰማይ ቤትም እናወርዳችኋለን ማለት ጀምረዋል። እንደዚህ አይነቱን በምድርም በሰማይም የረከሰ ቆሻሻነት የሚቀበል ትዕግስትም ሆነ ሆደ ሰፊነት በፍጹም ሊኖረን አይገባም። አባቶቻችን ያስተማሩንና በእኛም ዉስጥ በየቀኑ የሚያብበዉ የኢትዮጵየዊነት መንፈስ በገፉት ቁጥር የሚጠነክርና መልሶ የሚጋፋ አለት ነዉ እንጂ መዶሻ ባረፈበት ቁጥር የሚደረመስ የመንደር ዉስጥ ካብ አይደለም።

ትናንት አይናችን እያየ ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ አራሱን ነጻ የወጣዉ የኬንያ ህዝብ አሁንም በቅርቡ አንደገና አይናችን እያየ የዲሞክራሲ መብቱንና ሰብዓዊ ክብሩን በትግሉ አስከብሯል። የኬንያ ህዝብ ብሔራዊ ነጻነቱን የተጎናጸፈዉ የኛዉ አገር መሪ በሰጡት ድፕሎማሲያዊ ድጋፍና እርዳታ አንደሆነ እነሱም እኛም እናዉቃለን። ሆኖም ዛሬ ከኬንያ ህዝብ የነጻነትና የዲሞክራሲ ትግል የመማር ተራ የእኛ የኢትዮጵያዉያን ነዉ። ከድል በፊት በተደጋጋሚ መሸነፍ አንዳለና በዙዎች በሰላም እንዲኖሩ ጥቂት ሰዎች መሞት እንዳለባቸዉ የኬንያዉያን የአጭር ግዜ የትግል ታሪክ አሳይቶናል። እኛ ኢትዮጵያዉያን ደግሞ በተደጋጋሚ መሸነፍ ብቻ ሳይሆን የሰላምና የዲሞክራሲ ትግል ምዕራፋችን የብዙ ጀግኖቻችንን የህይወት መስዋዕትነት ጠይቋል። ከዛሬ በኋላ ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነዉ፤ እሱም ፍርሀታችንን ዉጠን ጠላታችንን ፊት ለፊት መግጠምና እንደ ኬንያዉያን ነጻነታችንን ማወጅ ነዉ። አለዚያ ፍርሀትን በሸሸነዉ ቁጥር እሱ ባቋራጭ እየመጣ ያገኘናል እንጂ በፍጹም አናመልጠዉም።

..........................................................................................

## የዘረኛው ወያኔ ወታደሮች የግራዚያኒን ሀውልት ግንባታ የተቃወሙ ኢትዮጵያዊያንን አሰሩ

የፋሽስት ኢጣሊያ መንግስት ወኪል በመሆን በአንድ ቀን ከ30 ሺ በላይ ኢትዮጵያውያንን በስድስት ኪሎ አደባባይ የጨፈጨፈውን የሮዶልፎ ግራዚያኒን ሀውልት ለማቆም እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ለመቃወም ከትናንት በስቲያ እሁድ በስድስት ኪሎ የተሰባሰቡ የባለራእይ ወጣቶች ማህበር አባላት፣ የሰማያዊ ፓርቲ አባላትና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በአረመኔው የወያኔ አገዛዝ ወታደሮች መታሰራቸውና ከፍተኛ እንግልትም የደረሰባቸው መሆኑ ታወቀ።

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ወታደሮች ታዋቂውን የህግ ባለሙያና ፖለቲከኛ ዶ/ር ያእቆብ ሀይለማርያምንና ፣ የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢ/ር ይልቃል ጌትነትን ለአንድ ቀን ካሰሩዋቸው በሁዋላ በመታወቂያ ዋስ መልቀቃቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ። ተያይዞ የደረሰን ዘገባ እንዳመለከተው ከእስረኞች መካከል አንዳንዶቹ ብሄር ተብለው ሲጠየቁ ኢትዮጵያዊ በማለት በመመለሳቸው ዘራቸው ሳይቀር እንደተሰደበ ታውቋል። ከዚሁ በተጨማሪም በርካታ ወጣቶች የኢሜል እና የፌስ ቡክ የሚስጢር ቁልፋቸውን (ፓስወርድ) እንዲሰጡ መገደዳቸውንም ለማወቅ ተችሎአል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ዶ/ር ያእቆብና ሌሎች ሰዎችም የታሰሩት ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ፈቃድ አልተጠየቀም በሚል ሰንካላ ምክንያት መሆኑን ታውቋል፣ ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሊቪዥን ኢሳት ከዶር ያቆብ ጋር ቃለምልልስ ያደረገ ሲሆን ዶር ያቆብ በቃለ ምልልሱ የወያኔ ወታደሮች የወሰዱባቸው እርምጃ የሚያመለክተው አገዛዙ ለግራዚያኒ ጠበቃ መቆሙን ነው ብለዋል። ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ኢሳት ከባለራእይ ወጣቶች ማህበር መሪ ወጣት ሀብታሙ አያሌው ጋር ባደረገው ቃለምልልስ ላይ ወጣት ሃብታሙ እንደተናገረው ለዚሁ ተቃውሞ ፈቃድ የጠየቁት ከ 14 ቀናት በፊት እንደነበር ገልጾ በታሰሩት ላይ የተደረገው ምርመራ ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንዳልነበረው አያይዞ ተናግሯል ፣ በመጨረሻም ወጣት ሀብታሙ ዛሬም አንድ አባላቸው ታስሮ እንደነበር ገልጾ ወዴት እየሄድን እንደሆን አናውቅም ብሎአል።

## ጀርመናዊዉ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በወያኔ ጫና ስራቸዉን ለመልቀቅ መገደዳቸዉ ተሰማ

የመቀሌ ዩኒቨርሲቲን ለረጅም ግዜ በፕሬዚዳንትነት የመሩት ጀርመናዊዉ ፕሮፌሰር ዩኪአም ሄርዚግ ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣኖች በስራቸዉ ላይ ጣልቃ እየገቡ ስላስቸገሯቸዉ የስራ መልቀቂያ ደብዳቤ ባስገቡ በሦስት ቀን ዉስጥ መቀሌን ለቅቀዉ ወደ አገራቸዉ መጓዛቸዉን መቀሌ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን ከሰሞኑ በላኩልን ዜና ገለጹ። ፕሮፌሰሩ ለምክትል ጠ/ሚኒስተር ደመቀ መኮንን ባስገቡት የስራ መልቀቂያ ደብዳቤ ላይ ስራቸዉን የሚለቅቁት ባጋጠማቸዉ የጤና ችግር ምክንያት እንደሆነ ቢገልጹም ለመቀሌ ዩኒቨርስቲ ቅርበት ያላቸዉ ብዙ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት ከሆነ ፕሮፌሰር ሄርዚግ ከኃላፊነታቸው የተነሱት በቅርቡ ዩኒቨርሲቲው ዉስጥ በተካሄደ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግምገማ ፕሬዚዳንቱ ሀላፊነታቸዉን አልተወጡም በሚል በተደረገባቸዉ ግፊት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

ፕሮፌሰር ዩኪአም ሄርዚግ ከዚህ ቀደም በሁለት የዩኒቨርስቲዉ ምክትል ፕሬዚዳንቶች አሿሿም ላይ ዩኒቨርሲቲውን በበላይነት ከሚመራው ቦርድ ጋር አለመግባባት መፍጠራቸው የሚታወቅ ሲሆን ሁለቱን ተሿሚዎች በተመለከተ ለቦርዱ የጻፉትን ደብዳቤ በአስቸኳይ እንዲቀለብሱ ማስገደዱ ይታወቃል። አንድ ስማቸዉ እንዳይገለጽ የጠየቁ የዩኒቨርሲቲዉ ከፍተኛ ባለስልጣን ቦርዱ ፕሮፌሰር ሄርዚግ ለምክትል ፕሬዚዳንትነት ያጩዋቸውን ግለሰቦች ሳይቀበልና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥበት ለሦስት ወራት ያህል ቆይቶ አሁን ግን ሃያ አራት ሰአት በማይሞላ ግዜ ዉስጥ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ለመሾም መቻኮሉ የሚገርመና ግራ የሚያጋባ ነዉ ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሊቀመንበር አቶ ቴድሮስ ሓጎስ ለዩኒቨርስቲዉ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንትነት በጻፉት ደብዳቤ ላይ እንደገለጹት ፕሬዚዳንት ሄርዚግ ከኃላፊነታቸው የተነሱት የትራንስፎርሜሽኑን ዕቅድ በሚገባ በስራ አልተገበሩም በሚል እንደሆነ ሲሆን ከእሳቸዉ ሌላ የዩኒቨርሲቲው ማኔጂንግ ዳይሬክተርና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ምክትል ፕሬዚዳንት ወልፍ ሻን ፊርክስንና በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ዶክተር ዩኢኪም ሌንገርትን ቦርዱ ከኃላፊነታቸው ማንሳቱን ምንጮች ተናግረዋል፡፡ ሁለቱም ጀርመናውያን ከኃላፊነታቸው የተነሱበት ምክንያትም የአቅም ማነስና የአፈጻጸም ችግር የሚል መሆኑንም የዩኒቨርሲቲው መምህራን ገልጸዋል፡፡

## ተባይ ሆኖ መኖር፤ ዘመን እስኪቀየር

(በዶሊያስ)

የትላትል ወረት፣ የተምች፣ የኩብኩባ፣
የምስጥ፣ የጉንዳኑ፣ የቁንቋን ደረመን በቤት ውስጥ ሲረባ፣
በአልጋ በመኝታ፣ በልብስ፣ በገላችን በመላ ሲገባ፣

እንቅልፍን መመኘት ለሙሉ ጤንነት፣
ሰላም ወጥቶ መግባት፣ ለሕይወት ተግባሮች ደፋ ቀና ማለት፣
ትዳር፣ ሕጻናትን፣ ኑሮን በአቋም መምራት፣

ሰላም ውሎ ማደር፣ መስራትና መማር፣
ከቶ አይታሰብም፤ ስቃይ ነው መከራ በአግረ ሙቅ መታሰር።

ተስቦ በሽታ በአገር፣ በሰፈሩ፣ በቀዬው ከገባ፣
ጣጣቴ፣ ኩፍኙ፣ የጂራፍ ገረፋው፣ አታሞ ድብደባ፣
ስቃይ ነው መከራ፤ እንደየሰፈሩ ባሕልና እቀባ።

ግና አሁን፣
ተመስገን፣
መዓቱ የራቀ፣ ምሕረቱ የበዛ፣
ፈጣሪ ይመስገን፤ ኩብኩባና ተምቹ ብዙም አይታይም በማሳ ሲነዛ።

ያ! ቀጣና ዘመን፤ ያ! የወራት ክፉ፣
የተምች የኩብኩባው፣ የተስቦው ሲያልፉ፣
ዘመን ያመጣቸው፤ ከተምች፣ ከኩብኩባው የባሰ የከፉ፣
ለየት ያለ "ቁንቋን" በመላ አገሪቱ ወያኔ ረገፉ።

እንደ ገብረ ጉንዳን፣
ሃገሩን፣ ሰፈሩን፣ ወንዙንና ዱሩን፣

በመላ ቆጥቁጠው፣
በዘር፣ በሀይማኖት፣ በጎሳ ለይተው፣
ድሃው ማንቁርት ላይ የዓሳ እሾሕ ሰክተው፣
ዋይ! ዋይ! ያሰኙታል እንቅልፍ ሰላም ነስተው።

በዶሮ ገላ ላይ የሰፈረ ቁንቋን፣
በእርቃን ሰውነት ላይ የተጋባ ትኋን፣

የወያኔ አገዛዝ፤ ሶስቱም አንድ ናቸው፣
ሲሹ ደም ምጥመጣ፣ አልያም ማሳበድ፣ የግል ተልእኳቸው።
ኑሮ ያሳበደው፣ የቀን-ግፍ ሳያንሰው፣
በቆሰለ ሕይወት፣ የእምነትን በርበሬ መጋት በየአፍንጫው፣
ከበደልም በደል፣ ከግፍም ንጹሕ ግፍ ታሪክ የማይሽረው።

ሰማኒያ፤ ዘጠና፣ መቶ ዓመት ብትገዙም፣
ሙታን ባያያችሁ፤ ዘመናት ቢረዝሙም፣
የደም ጣቶቻችሁ አሻራዎች ናቸው፤ ቀልመዋል አይለቁም።

አንድ ነች ኢትዮጵያ፤ ከጥንትም ጀምሮ፣
ድካም ነው ትርፋችሁ፤ ድሃ ከቆረጠ፣ ድምጥማጥ ያጠፋል አይቀርም ተቀብሮ።

ትናንት በሙስሊሙ፤ ዛሬ በኦርቶዶስ፣
መርዛችሁ ቢረጭም የዲያብሎስ መንፈስ፣
እኛ ግን ጽኑ ነን፤ ዘመን የማይሽረን፤ በኢየሱስ ክርስቶስ።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org